የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ–ኅዳር ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 12
ADDIS ABABA 3rd December, 2002


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፫፻/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር
አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ፱፻፶፱


CONTENTS


Proclamation No. 300/2002
Environmental Pollution Control
Proclamation ........................................ Page 1959


## አዋጅ ቁጥር ፫፻/፲፱፻፺፭
## የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር
## አዋጅ

አንዳንድ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ጥረቶች ልማቱን የሚቀለብስ ጎጂ አካባቢያዊ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ በመሆናቸው ፤

በአጠቃላዩ አካባቢን መጠበቅ ፤ በተለይም የሰውን ጤንነትና በጎ ሁኔታ እንደዚሁም የሕያዋንን ደሕንነትና የተፈጥሮን ሥነ ውበት ማቆየት የሁሉም ተግባርና ኃላፊነት በመሆኑ ፤

የመከላከያ ወይም የማስወገጃ እርምጃዎችን በመውሰድ በማሕበራዊና በኢኮኖሚያዊ ልማት ጥረቶች ሂደት የሚከሰተውንና የማይፈለገውን ብክለት ማስወገድ ሳይቻል መከላከል ተገቢ በመሆኑ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

### ክፍል አንድ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፫፻/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፤

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ ፤

፩/ "ባለሥልጣን" ማለት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

፪/ "ኬሚካል" ማለት ኤለመንት ፤ ወይም ያልተቀላቀለም ይሁን የተቀላቀለ ውሁድ ፤ ወይም ተቀምሞ በሰው የተሠራ ፤ ወይም ደግሞ ከተፈጥሮ የተገኘ ፤ ቁስአካል ነው፤

## PROCLAMATION NO.300/2002
## ENVIRONMENTAL POLLUTION CONTROL PROCLAMATION

WHEREAS, some social and economic development endeavors may inflict environmental harm that could make the endeavors counter-productive;

WHEREAS, the protection of the environment, in general, and the safeguarding of human health and well-being, as well as the maintaining of the biota and the aesthetic value of nature, in particular, are the duty and responsibility of all;

WHEREAS, it is appropriate to eliminate or, when not possible, to mitigate pollution as an undesirable consequence or social and economic development activities;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Environmental Pollution Control Proclamation No.300/2002".

2. *Definitions*

In this Proclamation:

1) "Authority" means the Environmental Protection Authority;
2) "Chemical" means an element or a compound whether by itself, or in a mixture or a preparation, whether manufactured or obtained from nature;

፫· "አግባብ ያለው መሥሪያ ቤት" ማለት ይህ ስያሜ የተጠቀሰበት ድንጋጌ በሚነካው ጉዳይ ላይ በሕግ የተሰጠ ኃላፊነት ያለው የፌዴራል ወይም የክልል የመንግሥት አካል ነው፤

፬· "ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት" ማለት በፌዴራል መንግሥት ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፣ እንዲሁም በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሲሆን በክልሉ ሕግ መሠረት የሚሰየም ፍርድ ቤት ነው፤

፭· "ፍሳሽ" ማለት ተጣርቶ ወይም ሳይጣራ ፣ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ቆሻሻ ውሃ ወይም ሌላ ቆሻሻ ፈሳሽ ወይም ጋዝ ነው ።

፮· "አካባቢ" ማለት በመሬት ፣ በከባቢ አየር ፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት ፣ በውሀ ፣ በህያዋን ፣በድምፅ በሽታ ፣ በጣእም ፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በስነ ውበት ሳይወሰን ፣ በተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና ያሉበት ቦታ ፣ እንዲሁም መጠናቸውን ወይም ሁኔታ ቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ሕያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ ተስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፤

፯· "የአካባቢ ተቆጣጣሪ ወይም ተቆጣጣሪዎች" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ /፩/ መሠረት የሚሰየመው አካል ነው፤

፰· "አደገኛ ነገር" ማለት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳይ የሚያደርስ ጠጣር ፣ ፈሳሽ ወይም ጋዝ ወይም ተክል፣ እንስሳ ወይም ረቂቅ ሕዋስ ነው ።

፱· "አደገኛ ቆሻሻ" ማለት ተፈላጊነት የሌለው ሆኖ በአካባቢ ወይም በሰው ደህንነት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማንኛውም ነገር ነው ።

፲· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፩· "በካይ" ማለት ፈሳሽ ፣ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ ፣ በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ፣

ሀ) ያረፈበትን የአካባቢ ክፍል ጥራት በመለወጥ ጠቀሜታ የመስጠት አቅሙን የሚያጓድል ፣ ወይም

ለ) በሰው ጤና ወይም በሌሎች ሕያዋን ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝን ፣ በሽታን ፣ ክርፋትን ፣ ጨረርን ፣ ድምፅን ፣ ንዝረትን ፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ክስተትን የሚያመነጭ ፣ ማንኛውም ነገር ነው፤

፲፪· "ብክለት" ማለት በዚህ አዋጅ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የተደነገገን ማንኛውንም ግዴታ ፣ ማዕቀብ ወይም ገደብ ጥሶ የማንኛውንም አካባቢ ክፍል ቁሳዊ ፣ ጨረራዊ ፣ ሙቀታዊ ፣ ንጥረ ነገራዊ ፣ ሥነሕይወታዊ ወይም ሌላ ባህርይን በመለወጥ የተፈጠረ ፣ በሰው ጤና ወይም በጎነት ወይም ደግሞ በሌሎች ሕያዋን ላይ አደገኛ የሆነ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፤

፲፫· "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯/፩/ የተመለከቱት የአገሪቷ ክፍሎች ማለት ሲሆን ፣ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአዲስ አበባ እንደዚሁም የድሬዳዋ አስተዳደሮችንም ይጨምራል ።

፲፬· "የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት "ማለት ለአካባቢና ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ወይም ቁጥጥር በክልሉ መንግሥት ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የክልል መንግሥት አካል ነው፤

፲፭· "መልቀቅ" ማለት በውል ታስቦም ይሁን ሳይታሰብ በካይን ወደ ማንኛውም የአካባቢ ክፍል መጨመር ነው።

## ክፍል ሁለት
## የብክለት ቁጥጥር

**የብክለት ቁጥጥር**

፩· ማንም ሰው ተገቢን የአካባቢ ደረጃ በመተላለፍ አካባቢን ሊበክል ወይም በሌላ ሰው በኩል እንዲበከል ሊያደርግ አይፈቀድለትም ።

፪· ሕግ በመተላለፍ ማንኛውንም በካይ ወደ አካባቢ በሚለቅ ሰው ላይ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት አስተዳደራዊ ወይም ሕጋዊ ዕርምጃ መውሰድ ይችላል።

3) "Competent Agency" means any Federal or Regional Government organ entrusted by law with a responsibility related to the subject specified in the provision where the term is used;

4) "Competent Court" means, in the case of the Federal Government, a first instance court and in the case of a national regional state, a court designated on the basis of the law of that state;

5) "Effluent" means waste water, gas or other fluid, treated or untreated, discharged directly or indirectly into the environment;

6) "Environment" means the totality of all materials whether in their natural state or modified or changed by humans, their external spaces and the interactions which affect their quality or quantity and the welfare of human or other living beings, including but not restricted to, land, atmosphere, weather and climate, water, living things, sound, odour, taste, social factors, and aesthetics;

7) "Environmental Inspector or Inspectors" means the body designated under Article 7(1) of this Proclamation;

8) "Hazardous material' means any substance in solid, liquid or gaseous state, or any plant, animal or micro organism that is injurious to human health or the environment;

9) "Hazardous Waste" means any unwanted material that is believed to be deleterious to human safety or health or the environment;

10) "Person" means any natural or juridical person;

11) "Pollutant" means any substance whether liquid, solid, or gas which directly or indirectly:

(a) alters the quality of any part of the receiving environment so as to effect its beneficial use adversely; or

(b) produces toxic substances, diseases, objectionable odour, radioactivity, noise, vibration, heat, or any other phenomenon that is hazardous or potentially hazardous to human health or to other living things;

12) "Pollution" means any condition which is hazardous or potentially hazardous to human health, safety, or welfare or to living things created by altering any physical, radioactive, thermal, chemical, biological or other property of any part of the environment in contravention of any condition, limitation or restriction made under this Proclamation or under any other relevant law;

13) "Region" means any of those parts of Ethiopia specified as such under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and, for the purpose of this Proclamation, includes the Addis Ababa and Dire Dawa Administrations;

14) "Regional Environmental Agency" means any regional government organ entrusted, by the government of that region, with responsibility for the protection or regulation of the environment and natural resources;

15) "Release" means placing any pollutant in the environment in any way be it intentionally or otherwise.

## PART TWO
## Control of Pollution

3. *Control of Pollution*

1) No person shall pollute or cause any other person to pollute the environment by violating the relevant environmental standard.

2) The Authority or the relevant Regional environmental agency may take an administrative or legal measure against a person who, in violation of law, release any pollutant to the environment.

፫· ብክለትን ወይም ሌላ አካባቢያዊ ጉዳትን ሊያስከትል በሚችል የተግባር መስክ የተሰማራ ማንም ሰው ፣ የቆሻሻ መመንጨትን ለማስወገድ ወይም ወደተፈላጊው መጠን ለመቀነስ በባለሥልጣኑ ወይም በሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ትዕዛዝ መሠረት በተገቢ ቴክኖሎጂና ሲቻልም ቆሻሻን መልሶ በጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስችሉ ዘዴዎች መጠቀም አለበት።

፬· ብክለትን ያደረሰ ማንኛውም ሰው፣ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በሚወስነው ሁኔታና የጊዜ ገደብ መሠረት አካባቢውን ከበካይ ማፅዳት፣ ወይም ለማፅጃ የወጣውን ወጪ መሸፈን አለበት።

፭· በጤና ወይም በአካባቢ ላይ አደጋ እንዳያስከትል ከሚያሰጋ የሥራ እንቅስቃሴ ሊመጣ የሚችል ጉዳትን ለመከላከል ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ድርጅትን እስከ መዝጋት ወይም ወደ ሌላ ቦታ እስከ ማዛወር የሚደርስ ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ መውሰድ ይችላል።

፬· ስለአደገኛ ቆሻሻ፣ ኬሚካልና ጨረር አመንጪ ቁስ አያያዝ

፩· ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ፈቃድ ሳይያዝ ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን ማመንጨት፣ ማስቀመጥ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ማምከን ወይም ማስወገድ የተከለከለ ነው።

፪· ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ መልሶ በጥቅም ላይ በማዋል፣ በማጓጓዝ፣ በማምከን ወይም በማስወገድ ሥራ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በአካባቢ ወይም በሰው ጤና ወይም በጎ ሁኔታ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ አለበት።

፫· ጨረር አመንጪ ቁስን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ከከርሰ ምድር ለማውጣት፣ ለማጣራት፣ ለማስቀመጥ፣ እንደዚሁም በአገር ውስጥ ለማሰራጨት፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ በጥቅም ላይ ለማዋል ወይም ለማስወገድ፣ አግባብ ካለው መሥሪያ ቤት ፈቃድ መገኘት አለበት።

፬· አደገኛ ተብሎ የተመደበን ወይም ለተወሰነ አገልግሎት ብቻ እንዲውል የተወሰነን ኬሚካል ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለመቀመም፣ ለማስቀመጥ፣ በአገር ውስጥ ለማሰራጨት፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ ወይም በጥቅም ላይ ለማዋል ከባለሥልጣኑ ወይም ደግሞ ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ወይም አግባብ ካለው ከሌላ መሥሪያ ቤት ፈቃድ መገኘት አለበት።

፭· አደገኛ የሆነ ወይም ለተወሰነ አገልግሎት የሚውል ኬሚካልን በመቀመም፣ በማምረት ወይም በማጓጓዝ ወይም በኬሚካሉ በመነገድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ኬሚካሉ በተገቢዎቹ ደረጃዎች መሠረት መመዝገቡን፣ መታሸጉንና ምልክት የተለጠፈበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፭· የከተማ ቆሻሻ አያያዝ

፩· የከተማ አስተዳደሮች የተቀናጀ የከተማ ቆሻሻ አያያዝ ሥርዓትን በማውጣት፣ የከተማ ቆሻሻ መሰብሰቡን፣ መጓጓዙን፣ እንደተገቢነቱም በጥቅም ላይ መዋሉን፣ መምከኑን ወይም ጉዳት እንዳያመጣ ተደርጎ መወገዱን ማረጋገጥ አለባቸው፣

፪· ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ጋር በመተባበር፣ ባለሥልጣኑ የከተሞች የቆሻሻ አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓቶችን ብቃት መመዘንና የአተገባበራቸውንም ውጤታማነት መገምገም፣ መከታተልና ማረጋገጥ አለበት።

፫· ለሕዝብ ክፍት የሆነ ቦታን የሚያስተዳድር ማንም ሰው፣ ምንጊዜም በቂና ተስማሚ የመፀዳጃ ቤት፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መገልገያዎች/በቦታው መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ አለበት።

3) Any person engaged in any field of activity which is likely which is to cause pollution or any other environmental hazard shall, when the Authority or the relevant regional environmental agency so decides, install a sound technology that avoids or reduces, to the required minimum, the generation of waste and, when feasible, apply methods for the recycling of waste.

4) Any person who causes any pollution shall be required to clean up or pay the cost of cleaning up the polluted environment in such a manner and within such a period as shall be determined by the Authority or by the relevant regional environmental agency.

5) When any activity poses a risk to human health or to the environment, the Authority or the relevant regional environmental agency shall take any necessary measure upto the closure or relocation of any enterprise in order to prevent harm.

4. *Management of Hazardous Waste, Chemical and Radioactive Substance*

1) The generation, keeping, storage, transportation, treatment or disposal of any hazardous waste without a permit from the Authority or the relevant regional environmental agency is prohibited.

2) Any person engaged in the collection, recycling, transportation, treatment or disposal of any hazardous waste shall take appropriate precaution to prevent any damage to the environment or to human health or well-being.

3) The importation, mining, processing, keeping, distribution, storage, transportation or use of radioactive substances shall be subject to a permit from the competent agency.

4) The importation, preparation, keeping, distribution, storage, transportation or use of a chemical categorized as hazardous or of restricted use, shall be subject to a permit from the Authority or the relevant regional environmental agency or from any other competent agency.

5) Any person engaged in the preparation, production, manufacturing or transportation or in trading in any hazardous or restricted chemical may ensure that the chemical is registered, packed and labeled as per the applicable standards.

5. *Management of Municipal Waste*

1) All urban administrations shall ensure the collection, transportation, and, as appropriate, the recycling, treatment or safe disposal of municipal waste through the institution of an integrated municipal waste management system.

2) In collaboration with the relevant regional environmental agency, the Authority shall monitor and evaluate the adequacy of municipal waste management systems and ensure the effectiveness of their implementation.

3) Any person responsible for the maintenance of any premise to which the public has access shall, at all times, ensure that adequate and suitable toilets and containers and other required facilities are provided for the disposal of waste.

፬· ባለሥልጣኑ ከየሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት እንዲሁም አግባብ ካላቸው ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር፣ የከተሞች የቆሻሻ ማስወገጃ መገልገያዎችን መገምገምና በአጥጋቢ ሁኔታ መሟላታቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት።

## ክፍል ሶስት
## ስለአካባቢ ደረጃዎች

፮· ስለአካባቢ ደረጃዎች

፩· አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር፣ ባለሥልጣኑ በሣይንሳዊና በአካባቢያዊ መርሆዎች ላይ የተመሠረቱና ተግባራዊ ለመሆን የሚችሉ የአካባቢ ደረጃዎችን ያዘጋጃል። እነዚህም ደረጃዎች ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፣

ሀ) ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾች ደረጃዎች፣

ለ) የአካባቢ አየር ጥራትን የሚገልፁና ለማይንቀሳቀሱና ለሚንቀሳቀሱ የአየር ብክለት ምንጮች የተፈቀዱትን የልቀት መጠኖች የሚወስኑ የአየር ጥራት ደረጃዎች፣

ሐ) ወደ አፈር የሚጨመሩ ኬሚካሎችን ወይም በአፈር ላይ ወይም ውስጥ የሚወገዱ ቁሶችን ዓይነትና መጠን የሚወስኑ የአፈር ጥራት ደረጃዎች፣

መ) የአሰፋፈር ሁኔታንና የአገሪቱ የሣይንስና የቴክኖሎጂ አቅምን በማገናዘብ የሚፈቀደውን ከፍተኛ የድምፅ መጠን የሚወስኑ የድምፅ ልቀት ደረጃዎች፣

ሠ) ለተለያዩ የቆሻሻ ዓይነቶች አመንጫጨት፣ አያያዝ፣ አከማቻቸት፣ አመካከን፣ አጓጓዝና አወጋገድ የሚያገለግሉ የመጠንና የአተገባበር ደረጃዎች።

፪· የሚያስከትለውን ጠንቅ ለመግታት በሚከረፋ ሽታ ምንጮች ላይ ቁጥጥር መካሄድ አለበት።

፫· ባለሥልጣኑ አካባቢን ለመጠበቅ ወይም መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ እንደአስፈላጊነቱ ለተለያዩ ሥፍራዎች የተለያዩ የአካባቢ ደረጃዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፬· ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት በየራሳቸው ልዩ ሁኔታ በመመሥረት በፌዴራሉ እርከን ከተወሰኑት የጠበቁ ደረጃዎችን አውጥተው በሥራ ላይ ሊያውሉ ይችላሉ። በፌዴራሉ እርከን ከተወሰኑት የላሉ ደረጃዎች እንዲያወጡ ግን አይፈቀድላቸውም።

፭· የሕዝብ ጥቅምን ለማጎልበት ሲባል አግባብ ያለውን የአካባቢ ደረጃ እንዲያሟሉ የሚጠበቅባቸውን የተወሰኑ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ተፈፃሚነት ባለሥልጣኑ ለተወሰነ ጊዜ እንዲታለፉ ሊፈቅድ ይችላል።

## ክፍል አራት
## ስለአካባቢ ተቆጣጣሪዎች

፯· ስለአካባቢ ተቆጣጣሪዎች

፩· የአካባቢ ተቆጣጣሪዎች /ከዚህ በኋላ "ተቆጣጣሪዎች" እየተባሉ የሚጠሩ/ በባለሥልጣኑ ወይም በሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይሰየማሉ፤

፪· ተቆጣጣሪዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ሥልጣንና ተግባራቸውን ሲወጡ ሥራቸውን በትጋትና ያለአድልዎ መፈፀም አለባቸው።

፰· የተቆጣጣሪዎች ሥልጣንና ተግባር

፩· የአካባቢ ተቆጣጣሪዎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፤

ሀ) የአካባቢ ደረጃዎችና ተዛማጅ ግዴታዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤

ለ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፮) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ ሳያሳውቁ ወይም ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳይዙ በማንኛውም ተገቢ መስሎ በሚታያቸው ጊዜ ወደ ማንኛውም ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ መግባት፤

4) The Authority shall, in collaboration with the relevant regional environmental agencies and any other competent agencies, monitor the situation with regard to the availability of waste disposal facilities and take the necessary measures to ensure that their availability is satisfactory.

## PART THREE
## Environmental Standards

6. *Environmental Standards*

1) In consultation with competent agencies, the Authority shall formulate practicable environmental standards based on scientific and environmental principles. The sectors that require standards shall include at least the following:
   (a) Standards for the discharge of effluents into water bodies and sewage systems.
   (b) Air quality standards that specify the ambient air quality and give the allowable amounts of emission for both stationary and mobile air pollution sources.
   (c) Standards for the types and amounts of substances that can be applied to the soil or be disposed of on or in it.
   (d) Standards for noise providing for the maximum allowable noise level taking into account the settlement patterns and the availability of scientific and technological capacity in the country.
   (e) Waste management standards specifying the levels allowed and the methods to be used in the generation, handling, storage, treatment, transport and disposal of the various types of waste.
2) Sources of noxious odour shall be regulated so that the nuisance they cause is prevented.
3) The Authority may prescribe different environmental standards for different areas as it may find necessary to protect or rehabilitate the environment.
4) National regional states may, based on their specific situation, adopt environmental standards that are more stringent than those determined at the Federal level. However, they shall not adopt standards which are less rigorous than those determined at the Federal level.
5) The Authority may, for a fixed period of time, authorize the waiver of the duty to comply with some requirements of specified environmental standards in order to promote public benefit.

## PART FOUR
## Environmental Inspectors

7. *Environmental Inspectors*

1) Environmental inspectors (hereinafter referred to as "inspectors") shall be assigned by the Authority or by the relevant regional environmental agency.
2) Inspectors shall exercise due diligence and impartiality in the discharge of their powers and duties under this Proclamation.

8. *Powers and Duties of Inspectors*

1) Inspectors shall have the following powers and duties:
   (a) ensure compliance with environmental standards and related requirements;
   (b) without prejudice to Sub-Articles (3) and (6) of this Article, enter any land or premises at any time which seems appropriate to them without prior notice or court order;

ሐ) ማንኛውንም ሰው ብቻውን ወይም በምስክር ፊት መጠየቅ፣

መ) ከብክለት ጋር ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ወረቀት፣ ማሕደር ወይም ሌላ ሠነድ መፈተሽ፣ መገልበጥ ወይም ለይቶ መቅዳት፣

ሠ) የማንኛውንም ቁስ ናሙናዎች እንደአስፈላጊነቱ ያለክፍያ መውሰድና በአካባቢ ወይም በሕይወት ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን መመርመር ወይም ማስመርመር፣

ረ) ይህ አዋጅ እና አግባብ ያለው ማንም ሌላ ሕግ መከበሩን ለማረጋገጥ ሸቀጥን፣ የአመራረት ሂደትን ወይም መገልገያን በፎቶግራፍ ማንሣት ፣ መለካት፣ መሳል ወይም መፈተሽ፣

ሰ) ይህን አዋጅ ወይም አግባብ ያለውን ሌላ ሕግ በመተላለፍ ጥፋት ተፈጽሞበታል የተባለ መሣሪያን ወይም ሌላ ነገርን መያዝ፣

፪· የተመደበው ተቆጣጣሪ የዚህን አዋጅ ወይም ማንኛውንም አግባብ ያለውን ሕግ ድንጋጌ ለተላለፈ ሰው የመተላለፉን ምንነት ይዘረዝርለታል፣ ይህንኑ መተላለፍ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለማስቀረት መውሰድ ያለበትን እርምጃ በመግለጽም እርምጃው እንዲወሰድ ሊያዝ ይችላል።

፫· የተመደበው ተቆጣጣሪ ማንኛውም እንቅስቃሴ በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ብሎ ሲጠረጥር እንቅስቃሴውን እስከ ማስቆም የሚደርስ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ትዕዛዝ ይሰጣል።

፬· ማንኛውም የተመደበ ተቆጣጣሪ በባለሥልጣኑ ወይም በሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የተሰጠ፣ የመሥሪያ ቤቱ ማህተም ያለበት መታወቂያ መያዝ ፣ ሲጠየቅም ማሳየት አለበት።

፭· ናሙና ሲወሰድ ባለንብረቱ የመገኘት ወይም ወኪል የመላክ መብት ስላለው ይህንኑ መብት እንዲያውቀው መደረግ አለበት።

፮· የሥራ አፈፃፀም ቅልጥፍናውን የሚበድልበት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የተመደበ ተቆጣጣሪ ወደ ማንም ድርጅት ቅጥር ግቢ ወይም ቦታ ሲገባ ለባለንብረቱ ማስታወቅ አለበት።

፱· ስለይግባኝ

፩· ተቆጣጣሪው በወሰደው ማንኛውም እርምጃ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው፣ እርምጃው ከተወሰደበት ቀን አንስቶ በአሥር ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ይግባኝ ማለት ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ውሳኔ ያልተሰጠ በመሆኑ ወይም የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ባለመሆኑ ቅር የተሰኘ ሰው ውሣኔው ከተሰጠበት ወይም የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን አንስቶ በሰላሣ ቀናት ውስጥ ክስ መመስረት ይችላል፣

፲· ስለ ማበረታቻ

፩· ብክለትን ለመከላከል ወይም መጠኑን ለመቀነስ በሚያስችል በማንኛውም ዘዴ መጠቀም ለሚጀምር ለማንኛውም ነባር ድርጅት የሚሰጥ ማበረታቻ በዚህ አዋጅ ሥር በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

፪· በባለሥልጣኑ ሲረጋገጥ ብክለትን ለመከላከል ሲባል ወደ አገር ውስጥ የሚገባ መሣሪያ ከገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ክፍያ ነፃ ይሆናል።

፲፩· ስለመክሰስ መብት

፩· ነገሩ የሚመለከተው መሆኑን ማስረዳት ሳይጠበቅበት፣ ማንኛውም ሰው በአካባቢ ላይ ጉዳት አድርሷል ወይም ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ተግባር እየፈጸመ ነው በሚለው በማንኛውም ሰው ላይ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል መሥሪያ ቤት ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው።

(c) question any person alone or in the presence of witnesses;

(d) check, copy or extract any paper, file or any other document related to pollution;

(e) take, free of charge, samples of any material as required and carry out or cause to be carried out tests to determine whether or not it causes harm to the environment or to life;

(f) take photographs, measure, draw, or examine any commodity, process or facility in order to ensure compliance with this Proclamation and with any other relevant law;

(g) seize any equipment or any other object which is believed to have been used in the commission of an offence under this Proclamation or any other relevant law.

2) When a person contravenes any of the provisions of this Proclamation or of any other relevant law, the inspector on duty shall specify the matter constituting the contravention and may also specify the measures that shall be taken to remedy the contravention within a given period of time.

3) When an inspector on duty suspects that any activity may cause damage to the environment, he shall order the taking of corrective measures upto the immediate cessation of the activity.

4) Every inspector shall have an identity card issued by the Authority or by the relevant regional environmental agency, bearing its official seal and show it when requested;

5) Whenever a sample is to be taken, the proprietor has the right to be present or to send his representative and he shall be informed accordingly.

6) When an inspector on duty visits an undertaking, he shall notify the proprietor unless he considers that such notification may be prejudicial to the efficient performance of his duty.

9. *Right to Appeal*

1) Any person dissatisfied with any of the measures taken by the inspector may appeal to the Head of the Authority or the relevant regional environmental agency, as the case may be, within ten days from the date on which the measure was taken.

2) Any person dissatisfied because no decision has been given as provided under Sub-Article (1) of this Article, or feels that the decision given is inappropriate, may institute a court case within thirty days from the date on which the decision was given or the deadline for decision has elapsed.

10. *Incentives*

1) Incentives for the introduction of methods that enable the prevention or minimizatin of pollution into an existing undertaking shall be determined by regulations issued hereunder.

2) Importation of new equipment that is destined to control pollution shall, upon verification by the Authority, be exempted from payment of custom duty.

11. *Right to standing*

1) Any person shall have, without the need to show any vested interest, the right to lodge a complaint at the Authority or the relevant regional environmental agency against any peron allegedly causing actual or potential damage to the environment.

፪· ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሣኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በውሳኔው ካልተስማማ ፣ ውሳኔው ከተሰጠበት ወይም የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን አንስቶ በስድሳ ቀናት ውስጥ በፍርድ ቤት ክስ መመሥረት ይችላል።

## ክፍል አምስት
## ጥፋትና ቅጣት

### ፲፪· ጠቅላላ

፩· ይህን አዋጅ ወይም አግባብ ያለውን ሌላ ሕግ የተላለፈ ፣ ነገር ግን ጥፋቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግም ሆነ በዚህ አዋጅ ቅጣት ያልተመደበለት ሆኖ የተገኘ ማንም ሰው ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ፣

ሀ) የተፈጥሮ ሰው ሲሆን፣ ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፣

ለ) በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሲሆን ከአሥር ሺህ ብር በማያንስና ከሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ የተፈፀመውን ጥፋት ማወቅ የነበረበትና ኃላፊነቱን በብቃት ያልተወጣው የሥራ ኃላፊ ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፣

፫· በወንጀኛ መቅጫ ሕግ መሠረት የከበደ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ፣ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት ቅጣቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

### ፲፫· ከተቆጣጣሪዎች ጋር በተያያዘ ስለሚፈፀሙ ጥፋቶች

፩· የተመደበ ተቆጣጣሪን ሥራውን እንዳያከናውን ያደናቀፈ ወይም ያሰናከለ ፣ ተቆጣጣሪው በሕግ መሠረት የጠየቀውን ወይም ያዘዘውን ያልፈፀመ ፣ በማስመሰል ተቆጣጣሪ ነው ሊባል የሞከረ ፣ ተቆጣጣሪው ወደ ማንኛውም ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ እንዳይገባ ወይም መዛግብት እንዳይመረምር ያደናቀፈ ማንኛውም ወረቀት፣ ማሕደር ፣ ወይም ሌላ ሰነድ እንዳይፈትሽ ፣ እንዳይገለብጥ ፣ ወይም ለይቶ እንዳይቀዳ የከለከለ ፣ ለተቆጣጣሪ መረጃ የከለከለ፣ ያሳሳተ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሰጠ ማንም ሰው ጥፋት ፈጽሟል፣

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ጥፋት የፈፀመ የተፈጥሮ ሰው ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ከሶስት ሺህ ብር በማያንስና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ ጥፋቱን የፈፀመው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ደግሞ ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ከብር አሥር ሺህ በማያንስና ከብር ሃያ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ የሥራ ኃላፊውም ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

### ፲፬· መዛግብትን በተመለከተ ስለሚፈፀሙ ጥፋቶች

አንድ ሰው በዚህ አዋጅ ወይም በሥሩ በሚወጡ ደንቦች መሠረት በመዝገብ እንዲያሰፍር የተጠየቀውን የእንቅስቃሴ፣ የምርት ፣ የቆሻሻ ዓይነት ባሕርይ ወይም መጠን ወይም ሌላ ተፈላጊ መረጃ በተገቢው ሳይመዘግብ ከቀረ ወይም በመዝገብ የሰፈረውን ከለወጠ ፣ ከአስር ሺህ ብር በማያንስና ከሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

2) When the Authority or regional environmental agency fails to give a decision within thirty days or when the person who has lodged the complaint is dissatisfied with the decision, he may institute a court case with in sixty days from the date the decision was given or the deadline for decision has elapsed.

## PART FIVE
## Offences and Penalties

### 12. *General*

1) A person who, under this Proclamation or under any other relevant law, commits an offence for which no penalty is provided for either in the Penal Code or under this Proclamation, is liable on conviction:

(a) in the case of a natural person, to a fine of not less than five thousand Birr and not more than ten thousand Birr or an imprisonment of not more than one year or both;

(b) in the case of a juridical person, to a fine of not less than ten thousand Birr and not more than twenty thousand Birr.

2) Where a juridical person is convicted pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the officer in charge who should have known the commission of the offence, and who failed to fulfill his duty appropriately shall be liable to a fine of not less than five thousand Birr and not more than ten thousand Birr or an imprisonment of not more than two years or both.

3) Unless the provisions of the Penal Code provide more severe penalties, the penalties laid down under this Proclamation shall be applicable.

### 13. *Offences Relating to Inspectors*

1) A person commits an offence if he hinders or obstructs an inspector on duty in the execution of his duty, fails to comply with a lawful order or requirement made by an inspector, impersonates an inspector, or refuses an inspector entry into any land or premise or hinders an inspector from getting access to records, prevents an inspector from checking, copying or extracting any paper, file or any other document, withholds, misleads or gives wrong information to an inspector.

2) A natural person who commits an offence under Sub-Article (1) of this Article is liable, on conviction, to a fine of not less than three thousand Birr and not more than ten thousand Birr, and, in the case of a juridical person, to a fine of not less than ten thousand Birr and and not more than twenty thousand Birr, and imprisonment of the officer in charge for a term of not less than one year and not more than two years or a fine of not less than five thousand Birr and not more than ten thousand Birr or both.

### 14. *Offences Relating to Records*

A person commits an offence if he fails to comply with this Proclamation or any regulations issued hereunder to keep records of activities or products or of the types, characteristics or amounts of waste or of any other information, or if he alters any record shall be liable, on conviction, to a fine of not less than ten thousand Birr and not more than twenty thousand Birr.

፲፭· <u>አደገኛ የሆነ ቆሻሻንና ሌላ ቁስን በተመለከተ ስለሚፈፀም ጥፋት</u>

፩· አንድ ሰው አደገኛ ቆሻሻን ወይም አደገኛ ነገርን አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ካልያዘ፣ መለጠፍ ያለበት ዝርዝርን አሳስቶ ከለጠፈ ወይም ጭራሹን ካልለጠፈ ፣ ወይም ደግሞ ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን፣ ወይም ሌላ ነገርን በተመለከተ መረጃ ከነፈገ ወይም ያልተፈቀደ የአደገኛ ቆሻሻ ዝውውርን ለማካሄድ ከሞከረ ወይም ካካሄደ ወይም ደግሞ እንዲካሄድ ለመርዳት ከሞከረ ወይም ከረዳ ጥፋተኛ ነው።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ጥፋት የፈፀመ የተፈጥሮ ሰው ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ከሃያ ሺህ ብር በማያንስና ከሃምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ ጥፋቱን የፈፀመው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ደግሞ ከሃምሳ ሺህ ብር በማያንስና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል። የሥራ ኃላፊውም ከሦስት ዓመት በማያንስና ከስድስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከሰላሳ ሺህ ብር በማያንስና ከሰባ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፲፮· <u>ብክለትን በሚመለከት ስለሚፈፀም ጥፋት</u>

አንድ የተፈጥሮ ሰው የዚህን አዋጅ ወይም በሥሩ የሚወጡትን ደንቦች በመተላለፍ በካይን ወደ አካባቢ በመልቀቅ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ፣ ከአንድ ሺህ ብር በማያንስና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል። ጥፋቱን የፈፀመው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከሃያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ፣ የሥራ ኃላፊውም ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፲፯· <u>ስለመውረስ እና ወደ ነበረበት ሁኔታ ስለመመለስ</u>

ይህን አዋጅና በሥሩ የሚወጡትን ደንቦች በመጣስ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ሰው ላይ ከሚወሰንበት ማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ፣

ሀ) ለጥፋቱ ተግባር የዋለ ማንኛውም ነገር ተወርሶ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ወይም በሌላ መንገድ እንዲወገድ፣

ለ) አካባቢውን የማፅጃ ወይም መካሪያውን ፣ ኬሚካሉን ወይም ዕቃውን የማስወገጃ ወጪ ተከሳሹ እንዲከፍል፣ እንደዚሁም፣

ሐ) ጉዳት የደረሰበትን አካባቢ ተከሳሹ በራሱ ወጪ ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመልስ ወይም ደግሞ ይህ የማይቻል ከሆነ ተገቢ ካሣ እንዲከፍል ማዘዝ ይችላል።

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፲፰· <u>*የመሸጋገሪያ ድንጋጌ*</u>

በሥራ ላይ ያሉ ተቋማት ይህን አዋጅ እንዴት ተፈፃሚ እንደሚያደርጉት በዚህ አዋጅ ሥር በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

፲፱· <u>*መረጃ የመስጠት ግዴታ*</u>

፩· የዚህን አዋጅ ወይም ከዚህ አዋጅ ጋራ ግንኙነት ያለውን የሌላ ሕግ ድንጋጌ የሚመለከት ተግባርን የሚያከናውን ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በሚፈልገው መሠረት የሥራ እንቅስቃሴውን መረጃ ማቅረብ አለበት።

ባለሥልጣኑ ማንኛውንም አካባቢን የሚመለከት መረጃ የማግኘት መብት አለው።

15. *Offences Relating to Wastes and Other Materials that are Hazardous*

1) A person commits an offence if he fails to manage a hazardous waste or another substance according to the relevant laws, mislabels or fails to label or in any way withholds information about any hazardous waste or other material or attempts to take part or takes part or attempts to aid or aids in the illegal traffic of any hazardous waste or other material.
2) A natural person who commits an offence under Sub Article (1) of this Article is liable, on conviction, to a fine of not less than twenty thousand Birr and not more than fifty thousand Birr and in the case of a juridical person to a fine of not less than fifty thousand Birr and not more than one hundred thousand Birr, and to a term of imprisonment of the officer in charge of not less than five years and not more than ten years, or a fine of not less than five thousand Birr and not more than ten thousand Birr of both.

16. *Offences Relating to Pollution*

A natural person commits an offence if he discharges any pollutant contrary to the provisions of this Proclamation or regulations issued hereunder and is liable, on conviction, to a fine of not less than one thousand Birr and not more than five thousand Birr or to an imprisonment of not less than one year and not more than ten years or both and, in the case of a juridical person, to a fine of not less than five thousand Birr and not more than twenty five thousand Birr and an imprisonment of the officer in charge for a term of not less than five years and not more than ten years, or a fine of not less than five thousand Birr and not more than ten thousand Birr or both.

17. *Forfeiture and Restoration*

The court, before which a person is prosecuted for an offence under this Proclamation or regulations issued hereunder, may, in addition to any penalty it impose upon the convicted person, order:

(a) the confiscation of any thing used in the commission of the offence in favor of the state or to dispose of it in any other way;
(b) that the cost of cleaning up and the disposing of the substance, chemical or equipment seized be borne by the convicted person; and
(c) the convicted person to restore to the state in which the environment was prior to the infliction of the damage, and when such restoration is not possible to pay appropriate compensation.

## PART SIX
## *Miscellaneous Provisions*

18. *Transitory Provision*

Regulations to be issued hereunder shall determine the manner in which existing undertakings shall comply with this Proclamation.

19. *Duty to Provide Information*

1) Any person engaged in an activity pertaining to any of the provisions of this proclamation or any other related law shall provide any information on his activity as required by the Authority or the relevant regional environmental agency.
2) The Authority shall have access to all environmental data and information.

፳· <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፳፩· <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>
ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ የሆነ ሕግ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፳፪· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

20. *Power to Issue Regulations*
The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the effective implementation of this Proclamation.

21. *Inapplicable Laws*
Any law or practice inconsistent with this Proclamation is inapplicable regarding matters provided herein.

22. Effective Date

This Proclamation shall come into force as of the 3rd day of December, 2002.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of December, 2002.

**GIRMA WOLDE GIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**